የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት

ልሣነ ህግ ጋዜጣ

22ኛዓመት ቁጥር 140
አሶሳ ሐምሌ/ 2008 ዓ.ም

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት
ምክር ቤት

ጠባቂነት የወጣ አዋጅ

22ኛ ዓመት ቁጥር 140
አሶሳ ሐምሌ/ 2008 ዓ.ም

## <u>አዋጅ ቁጥር140/2008 ዓ.ም</u>

## <u>የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት</u>

## <u>የግዥና ንብረት አስተዳደር ለማሻሻል የወጣ አዋጅ /መሻሻያ/</u>

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት የግዥና ንብረት አስተዳደር ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 96/2003 ዓ.ምን ማሻሻል አስፈሊጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት በተሻሻለ□ ሕ□መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 ተራ ቁጥር 1 በተሰጠዉ ሥልጣን መሠረት የሚከተለዉ ታዉጇል፡፡

### <u>አንቀጽ 1</u>
### <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ “የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት የግዥና ንብረት አስተዳደር /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር 140/2008ዓ.ም” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 2

## ማሻሻያ

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት የግዥና ንብረት አስተዳደር ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 96/2003 ዓ.ምን እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

በአዋጁ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 4 ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ 5 ተጨምሯ፡፡

" 5. በአዋጁ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተመለከተዉ ቢኖርም በክልሉ የተቋቋሙ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት በጫራታ ዉድድር ዉስጥ ካሉ ለክልሉ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅሞች ሲባል በየደረጃዉ አቅማቸዉ እየተገመገመ ለክልሉ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋም ቅድሚያ ይሰጣል ወይም ለክልሉ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋም የአከባቢ ግልጽ ጨረታ ይወጣል፡፡ ዝርዝሩ ቢሮዉ በሚያወጣዉ መመሪያ መሠረት ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 3

## አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከ-----ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አሶሳ----ቀን 2008 ዓ.ም

አሻዲሊ ሀሰን አልአጀብ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት

ፕሬዝዳንት